# ሠላማዊ የሥልጣን መተካካት፤ ለሀገሪቱ ልማት ቀጣይነት

**ጌቱ አያልነህ**

ከሁለት ዓመት በፊት በመስከረም ወር ላይ አዳማ ከተማ ላይ በተካሄደው የኢህአዴግ ምክር ቤት ስብሰባ የኢህአዴግ ሊቀመንበር እና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የመተካካትን መርሆ ይፋ አደረጉ፡፡ ፓርቲውም ባወጣው የመተካካት መርሆ (ስትራቴጂ) ላይ ተወያይቶ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከነበሩ አንጋፋ አመራሮች መካከል አንዳንዱን ለአዲሱ ትውልድ የኢህአዴግ አባላት ለማስረከብ በመወሰን አፀደቀ፡፡

የዚህ ውሣኔ መሠረታዊ ዓላማ ወጣቱ ትውልድ በድርጅቱ ውስጥ ገብቶ በመንቀሳቀሱ ከፓርቲው አመራር አካላት በመማርና ልምድ በመቅሰም፣ መስዋዕትነት በመክፈል፣ ለኃላፊነት እንዲበቃና ለድርጅቱ ህልውና እንዲተጋ ለማስቻል ነው፡፡

ከዚህ ውሣኔ በኋላ አዳዲስ አባላት በተለያዩ ተቋማት በኃላፊነት ደረጃ እና በሚኒስትርነት ደረጃ ተመድበው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ደረጃ የተሾሙት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን ቀደም ሲል በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነትና በውጪ ጉዳይ ሚኒስትርነት ደረጃ ተሹመው የመተካካት መርሆው የመጀመሪያው ሰው መሆን ችለዋል፡፡ ኃላፊነታቸውንም በብቃት ሲወጡ ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አሥር ዓመታት በአገሪቱ የተገኙት አዳዲስ ለውጦች የኢህአዴግ አንጋፋ አመራሮች ከአዳዲስ አመራር አባላት ጋር ያስመዘገቧቸው ድሎች ናቸው፡፡

ያልታሰበውና ድንገተኛው የቀድሞው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕልፈተ ህይወት በመላው አገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ኃይማኖት፣ ብሔር፣ ጾታ፣ ድንበር ሳይለይ፣ በሕዝቡ ዘንድ ከባድ ድንጋጤና የሀዘን ስሜት ፈጥሯል፡፡

የመለስ አስክሬን አዲስ አበባ በገባበት ወቅት ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ ሕዝቡ መንገዱን ሞልቶና ዘግቶ የዝናቡ ውሽንፍር፣ የሌሊቱ ቁር ሳይበግረው ጧፍ እያበራ ረዥሙን መንገድ በእግሩ ተጉዞ አስክሬኑን ተከትሎ ያለውን ፍቅር አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ የአቶ መለስ ህልፈተ ሕይወት ከተገለፀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሥርዓተ ቀብራቸው ፍፃሜና ብሔራዊ የሀዘን ቀኑ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ በመላቀስ ለመሪው የነበረውን ጥልቅ ፍቅር ገልጿል፡፡ ሀዘኑን ለመግለፅ አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሉ ግልብጥ ብሎ አደባባይ የወጣው ሕዝብ በመለስ ዜናዊ በሣል አመራርና በሕዝቦች ያላሰለሰ ተሳትፎ ባለፉት ዓመታት በፖለቲካ፣ በምጣኔ ሀብት እና በማህበራዊ መስኮች በአገሪቱ በርካታ ውጤቶች መመዝገባቸውን መስክሯል፡፡

በታላቅ ሥነ ሥርዓት እና በመልካም ሥነ ምግባር ሀዘኑን የገለፀው ይህ ሕዝብ ሀዘኑን የገለፀው ተገዶ ሳይሆን ድህነትን ለማጥፋት የተከናወኑት ሥራዎች ወዶ ፈቅዶ እንዲወጣ አስገድደውት ነው፡፡

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ምክትል ሆነው ሲሰሩ የቆዩት አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ አቶ መለስ ዜናዊ የህክምና ክትትል ላይ በነበሩበት ወቅት፣ እሳቸውን ተክተው አገሪቱን በመምራት የአመራር ክፍተቱን በብቃት ሲሸፍኑ ቆይተዋል፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ አንዳንድ የውጪ ኃይሎች፣ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የተፈጠረውን ክፍተት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በትረ ሥልጣኑን ለመጨበጥ በመቋመጥ ልዩነትን ለማራገብ ጥረት አድርገዋል፡፡

ለዚህም ኢህአዴግ ውስጥ የተከሰተው የአመራር ክፍተት ለመሙላት ስምምነት አልተፈጠረም፣ የሥልጣን ሽኩቻ በመባባሱ ምክንያት አገሪቷ ለመበታተን አደጋ ደርሳለች፣ አመራሩንም ነባር ታጋዮች ከእጃቸው ማስወጣት አልፈለጉም፣ የኃይማኖትና የብሔር ግጭት ሊፈጠር ነው የሚሉና የመሳሰሉ አሉባልታዎች ሲናፈሱ ከርመዋል፡፡

ባለፈው ዓርብ መስከረም 11 ቀን 2005 ዓ.ም የተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ግን አሉባልታው ከአሉባልታነት እንደማያልፍ ያስመሰከረ ውሣኔ አሳልፏል፡፡

ምክር ቤቱ ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾሟል፡፡ አቶ ደመቀ መኮንን ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የትምህርት ሚኒስትር በማድረግ ሹመታቸውን በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የአቶ መለስ ዜናዊ ሕልፈትን ተከትሎ ሕዝቡ በየአደባባዩ የገለፀው ስሜት በአገሪቱ ምጣኔ ሀብት፣ ፖለቲካና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ለውጥ መምጣቱን ያሳየ ነው፡፡ በተለይ በአባይ ወንዝ ላይ እየተካሄደ ያለው የስድስት ሺህ ኪሎ ዋት የህዳሴው ግድብ ኃይል ማመንጫ ግንባታ የአገሪቱን ዜጎች ሁሉ "እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ" አድርጎ ያሰባሰበ ነው፡፡ ሕዝቡ የሀዘን ስሜቱን በገለፀበት ወቅት የህዳሴውን ግድብ ሥራ እንደተጀመረ እናጠናቅቀዋለን በማለት አቋሙን ገልጿል፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በክልል ከተሞች እየተሰሩ ያሉት የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታዎች፣ በአክሲዮን ልማት ማኅበር በተደራጁ ዜጎች፣ በሀገር ውስጥ እና በውጪ ባለሀብቶች እየተገነቡ ያሉ ህንፃዎች ለብዙ ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ ግንባታቸው የተጠናቀቁት ህንፃዎች ደግሞ ለመኖሪያ ቤትነትና በንግድ ተቋምነት ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ የነዋሪውን ሕዝብ ኑሮ ዘመናዊ ከማድረግ አልፈው ለከተሞች መስፋፋትና ውበት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ እንደ አዲስ አበባ በመሳሰሉት ከተሞች የተገነቡት የጋራ መኖሪያዎች በትንሽ መሬት ብዙ ዜጎች ማሰባሰብ ችለዋል፡፡ የዜጎችን የአኗኗር ስልት ለውጠዋል፣ ለከተሞች ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በከተሞች እየተሰሩ ያሉ የኮብል ስቶን መንገድ ሥራዎች፣ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ድረስ እየተሰሩ ያሉ የትምህርት ቤት ተቋማት በየክልሉ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት የተካሄዱት ግንባታዎች፣ የጤና ተቋማት ሥርጭት በአርብቶ አደሩና በአርሶ አደሩ አካባቢ ተስፋፍቷል፡፡ በዚህም 15 ሺህ የሚደርሱ ጤና ኬላዎች በገጠር ቀበሌዎች ተገንብተዋል፡፡ በየቀበሌው ለአንድ ጤና ኬላ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሰልጥነው እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ግብ በመጠናቀቁ በከተሞች የጤና ኤክስቴንሽን መርሐ ግብር ተቀርፆ የጤና ኬላ ግንባታዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች በሕዝቡ ውስጥ ጥልቅ የፍቅር ስሜት የፈጠሩ ናቸው፡፡ ይህንንም አቶ መለስ ዜናዊ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ ሀዘኑን በተለያየ ስልትና በለቅሶ ጭምር በማሳየት ገልጿል፡፡ ሕዝቡ ሀዘኑን የገለፀበት ስልት ሕዝብና መንግሥት አንድ መሆናቸውንና እጅና ጓንት ሆነው ለሀገር ልማት መስፋፋት፣ ለብሄራዊ መግባባትና ለገፅታ ግንባታ እየሰሩ መሆናቸውን ለዓለም ሕዝብ ያሳየ ነው፡፡ ሕዝቡ አጥብቆ ልማቱንና ሠላሙን የሚፈልግ ነው፡፡ በአስፈፃሚ አካላቱ ላይ እምነት ያለው ሕዝብ ነው፡፡ በአሉባልታ ሕዝቡን ለመከፋፈል ቢፈልግም ሕዝቡ ግን "ጆሮ ዳባ ልበስ" ብሎ ትኩረት እንዳልሰጠው አሳይቷል፡፡

የመለስ ሕልፈት በሕዝቡ ዘንድ ሥርዓተ አልበኝነትን ሳይፈጥር፣ በአመራር አካላትም የሥልጣን መሻኮት ሳይኖር፤ ሕዝብና መንግሥት መሪያቸውን በሦስት ሺህ ዘመናት የአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ባማረና በሰመረ መልኩ የቀብር ሥነ -ሥርዓቱን አከናውነዋል፡፡ የአመራር ክፍተቱን ለመሙላት የመተካካት ሥርዓቱ በሚፈቅደው መሠረት ተካሂዷል፡፡ ትምክህተኛና ጥገኛ ለሆኑ ኃይሎችና ክስተቱን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ልዩነቱ ማራገብ ለሚፈልጉ ሰዎች የሕዝቡ ስሜት አስደንግጧቸዋል፡፡ ሕዝቡ ከእነርሱ ጋር እንዳልሆነም አስረድቷቸዋል፡፡

ይህ ደግሞ ከቀድሞው የመለስ ህልፈት በኋላ ለከተሞች ሥርዓተ አልበኝነት፣ በገጠር አካባቢዎች የጎሳ እና የኃይማኖት ግጭት በአመራር መካከል የሥልጣን መሻኮት ይፈጠራል እያሉ ሲያናፍሱ ለነበሩት አካላት ተስፋ እንዲቆርጡ፣ መለስ ብለው አቋማቸውን እንዲያዳምጡ ያስገደደ ክስተት ሆኖ አልፏል፡፡ ብሔራዊ የሀዘን ስሜቱ ምንም ዓይነት ሥርዓት አልበኝነት ሳይከሰት ኮሽታ ሳይኖር በአግባቡ ተፈፅሟል፤ የሥልጣን መተካካቱም ተከናውኗል፡፡ ሕዝብ ተበጠበጠ አገር ተናወጠ ሲሉ ለነበሩ አካላት ምንም ነገር ሳይፈጠር የወትሮው እንቅስቃሴ መቀጠሉን ሕዝቡ አሳይቷቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምንም በላይ ከራሱ ጥቅም ይልቅ አገሩን እንደሚያስቀድም ገልጿል፡፡  ሠላምና ልማት አጥብቆ የሚፈልገው ሕዝቡ ከሚያሴሩ ሰዎች ጋር ሳይሆን ከሚሰሩ አካላት እንደሚቆም በተግባር ጭምር አስረድቷል፡፡

በትግሉ ውስጥ ያልነበሩ ሰዎች በአመራርነት መመረጣቸው የአቶ መለስን ዓላማ ያሳካ ነው፡፡ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማስፈጸም ብቃት ያላቸው ናቸው፡፡ ዕቅዱንም ማዕበል የሆነውን ሕዝብ በማስተባበርና በማንቀሳቀስ አሳክተው አገሪቷን ለለውጥ ያበቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የመተካካት ሥርዓቱ ለብዙ የአፍሪካ አገሮች አርአያ ነው፡፡ ሂደቱም ለምዕራባውያን ግርምት የፈጠረና ያስደመመ ሆኖ

አልፎአል፡፡ የሥልጣን መተካካቱ ኢህአዴግ የሁሉም ኃይማኖት እና ብሔር ፓርቲ መሆኑን ያስመሰከረ ነው፡፡

አንዳንድ ጥገኛ ትምክህተኛ የሆኑ ኃይሎች የኢፌዴሪ የተወካዮች ምክር ቤት ሹመቱን ቢያፀድቅም ኃላፊነቱን የተቀበሉት አመራሮች የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ለማስፈፀም እና አቅጣጫ ለመስጠት ሊከብዳቸው ይችላሉ ይላሉ፡፡ ይህ ግን ተቀባይነት የሌለው አመለካከት ነው፡፡ በሥልጣን መተካካቱ የተሾሙት አካላት ቀደም ሲልም ከአንጋፋ አመራር ሥር ሆነው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ሊሳሳቱ ሊወድቁ ቢችሉ እንኳን ከስህተታቸው እየተማሩ ይቀጥላሉ፡፡ አመራሩም የሚከናወነው ጥምረት (ኮኔክቲቭ) ባለው መልኩ ነው፡፡ የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱንም ሕዝቡን ይዘው በማንቀሳቀስ አገሪቷን በመምራት ለለውጥ ያበቃሉ፡፡

በመሆኑም አገሪቷን በአሥር ዓመት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ በሚደረገው ጥረት የተካሄደው ሠላማዊ የሥልጣን መተካካት የሀገሪቱ ልማት ቀጣይነት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡